# ኢህዴን ወይስ ሕወሀት ቁጥር 2?

በ 1983 ኢትዮጵያ በሕወሀት ስር ስትወድቅ በምራባዊያን ግፊት የፌደራል ስራአት እንዲኖራት መደረጉ ይታወሳል። ታዲያ 17 አመት ደምቼ ወታደራዊውን መንግስት የጣልኩት እኔ ስለሆንኩኝ ስልጣን ከእጄ አይወጣም ላሉትና ትግራይ ላይ ነጻ አገር የመመስረት ራእይ ላነገቡት ወያኔዎች ማእከላዊ የፖለቲካ ስልጣን ተበረከተላቸው። እነርሱም በምናውቃቸው የውጭ ሀይሎች ተቀምሮ የተሰጣቸውን በብሔርና ቋንቋ ላይ መሰረቱን ያደረገ የውስጥ አስተዳደር ክልሎችን በማዋቀር አገሪቱን ቀስ በቀስ የማፈራረስ ጉዞ ጀመሩ።

እዚህ ላይ ሁላችንም እንደምናስታውሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ የት መካለል ትፈልጋለህ ተብሎ ጥያቄ እንዳልቀረበለትና ሁሉም ነገር በሕወሀትና በዚያን ወቅት አብረውት ላይ ታች ይሉ በነበሩት ጸረ ኢትዮጵያዊ ሀይሎች ሽአቢያና ኦነግ ፍላጎት እንደ ቅርጫ ስጋ ብትንትኑ ወጥትዋል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ለትግራዊ መንግስት እንዲያገለግሉ ረቂቅ በሆነ መንገድ የአገሪቱን መፈራረስ ይመኙ የነበሩና በጎጠኝነት የሚታወቁ ግለሰቦችንና ድርጅቶች በአዲስ መልክ በማደራጀት ክልሎችን በሕወሀት መመሪያ እንዲያስተዳድሩና ሕዝቡም ከኢትዮጵያዊነት በፊት ጎጠኝነትን እንዲያመልክ ሀላፊነት ተሰጥቶአቸው ዙፋን ላይ ተኮፍሰው ተቀመጡ።

ይህ ሁሉ ሲሆን አማራውን እወክላለው ብሎ አንድም ግዜ ተንፍሶም ሆነ ተንቀሳቅሶ የማያውቀው ኢህዴን ተጎማምዶ መያዢያና መጨበጫው የማይታወቀውንና የአማራው ክልል ተብሎ የተሰየመውን እንዲገዛ በወያኔ ዘውድ ጠለቀለት። ልብ ብላችሁ አስቡ። ይህ ቡድን የፌደራሉ ስራት ሲዋቀርና ሁሉም ይሄ ግዛት የኔ ብሔር ነው እያለ ሲናቆር ብሎም ወኪል ያልነበራቸው ጎጃም፣ በጌምድርና ሰሜን፣ ወሎና ሸዋ ለመለየት በማይቻል መልኩ ብጥስጥሳቸው ሲወጣ የበይ ተመልካች ሆኖ ሲቀመጥ ካለው አላማ ውጪ ስልጣኑ ለምን ተሰጠው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። አይኑ ለሚያይ ጆሮው ለሚሰማና ሕሊና ላለው ሁሉ ምክንያቶቹ ግልጽ ይመስሉኛል።

አንደኛ ኢህዴንን ወይም አሁን ሌላ መጠሪያ ያጠለቀውን ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ዋና ሆነው የሚያሾሩት በሙሉ የክልሉ ተወላጆች አይደሉም። በተለያዩ የጥቅም ጉዳዮች የተባረሩትን ጨምሮ እስካሁን ያሉትን ሰዎች ስንመለከት የከምባታ፣ የሲዳማ፣ የኦሮሞ፣ የትግሬና ኤርትራዊ ጎሳዊ መሰረት እንዳላቸው እንገነዘባለን። "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንደሚባለው እንዚህ ሰዎች በሙሉ ትግል ውስጥ የገቡት በነርሱ ቋንቋ "የአማራውን የጭቆና አገዛዝ ለማውደምና ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል እስከመገንጠል እንዲወስኑ ለማድረግ" ስለነበር እንደ ገጸ በረከት ላገኙት ክልል ሕዝብ ጥላቻ እንጂ ቤሳ ቤስቲን ፍቅር እንድሌላቸው ወያኔ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው።

ለዚህም ነበር ለልማት በሚል ሽፋን ከሸዋ መናገሻ፣ ደራ፣ ቅምብቢትና የከሰም በረሀ ለኦሮሞና አፋር ሽልማት ሲሰጡ አማራው ትምክህተኛና ጨቋኝ ስለነበር ልማት ምን ያሸዋል በሚለው የግድ የለሺነት አቋማቸው የጸኑትና ምንም ያልተናገሩት። ትግራይ ደግሞ ተከዜን ተሻግራ ሁመራን፣ ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ ጠለምትን ከጎንደር ስትወስድ በተጨማሪም አፍላን፣ ራያንና አላማጣን ወዘተ ከወሎ ጎምዳ ጉያዋ ስትጨምር ኢህዴኖች በዝምታ ያለፉት። መተከልም ቤኒሻንጉል ነው ሲባል ታዲያ ምን ችግር አለ በሚል ሰጥ ለጥ ብለው የተቀመጡት።

ገና የኢህዴኖች ጉድ በዚህ ብቻ ያልቃል ብሎ የሚያስብና ከመቆየት የተነሳ ክልሉን ይታደጋሉ በሚል ልቡን የሚሰጣቸው አማራ ካለ የዋህ ብቻ ሳይሆን ቂሎ ማሞና በግም ጭምር የሆነ ብቻ ነው። በ 23 አመት ውስጥ ራስ ዳሽንን አሳልፎ የሰጠ፤ ከ 60 ሺህ በላይ መጤ ትግሬዎችን በመተማና በምራብ አርማጭሆ በማስፈር አማራውን ካገሩ ያባረረውና ለትግሬዎቹ መተማ ዮሀንስ ብሎ ከተማ የሰየመው የአማራ ጠላት እንጂ ሌላ ምን ስም ሊሰጠው ይገባል። እነዚህ መጤዎች እኮ ባሁኑ ወቅት አገሩ የኛ ስለሆነ ከትግራይ መካለል አለብን ብለው በአደባባይ አይን አውጥተው ጥያቄ ብቻ ሳይሆን መሳሪያ አንግበው ተነስተዋል። አድምጣችሁት እንደሆነ ባላውቅም በአይጋ ፎረም ገዱ አንዳርጋቸው በጥር መጨረሻ በሰጠው ቃለ ምልልስ በትግራይና በአማራ መካከል" እስካሁን ድረስ ድንበር አልተካለለም፤ እነዚህ መሬቱ የኛ ነው ይላሉ እነዚያም የኛ ነው ይላሉ" በሚል አነጋገር ሁኔታውን አቃሎና በኢህዴን በኩል አካባቢውን ለትግራይ አሳልፎ ለመስጠት ውስጥ ውስጡን መወሰኑን አረጋግጡዋል። ይህንኑ ቃለ መጠይቅ የጥር ወር አይጋ ፎረምን ገጾች ብታፈላልጉ ታገኙታላችሁ። የፌብሩዋሪ ወርን የመጀመሪያ ሳምንቶች መመልከትም ሊረዳ ይችላል።

በሁሉም ክልሎች ከሕወሀት በተጨማሪ ለጎሳ ታሪኮችና ቋንቋዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የት/ት ስራት እውን ሆኖአል። በአማራ ክልል የሚሰራው ዋግን፣ አዊንና የወሎ ኦሮሞን ለማስገንጠል ኢህዴን የሚተገብራቸው እቅዶችን በመመልከት ድርጅቱ ጸረ አማራ ስለ መሆኑ ማረጋገጥ አይከብድም። በነዚህ ዞኖች ት/ትና አስተዳደር ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ አማርኛ ቦታውን እንዲያጣ እየተገፋና እንደ ጠላት እየተቆጠረ በመሄድ ላይ ይገኛል። በክልሉ አሁን ያሉትን ባለስልጣኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ንግግር ሲያደርጉ ብታዳምጡ ከአማርኛው ውስጡ የሚሽጎጡት የ እንግሊዝኛ ቃላቶች ብዛት ያስገርማል። ጭራሽኑ ለምን በፈረንጆቹ ቋንቋ ቢጠቀሙ ይሻል ነበር ያስብላል። የአማራው ሕዝብ እንደሆነ እነርሱ የሚሉትን ምንም ስለማይገባው "ተከድኖ ይብሰል" በሚል ልፍለፋቸው ገብቶት ያዳመጠ ለመምሰል ዝም ብሎ ያጨበጭብላቸዋል።

ከዚህ ቀደም ማለትም የዛሬ 5 ና 6 አመት ገደማ የቀድሞዋ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት በቤዛዊት የቀዳማዊ ሀይለስላሴ ቤተ መንግስት ውስጥ ስለ አማራ ታሪክና ቋንቋ የሚያጠና ተቋም ለመመስረት ሞክራ ግራ የተጋባች አባል መሆንዋ ላይ ግምገማ ተደርጎ ሴትየዋም አምባሳደር እንድትሆንና ያቀረበችውም ሀሳብ መሬት እንዳይነካ ውሳኔ የተሰጠበት ምክንያት ኢህዴን ስለ አማርኛና የአማራ ታሪክ መጥፋት ቆርጦ መነሳቱን የሚያረጋግጥ ሀቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

ታሪክን በተመለከተ አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ። አጼ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን እንደገና አንድ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የቀድሞው ካሳ ምርጫ በሁዋላ ደግሞ አጼ ዮሀንስ ከ እንግሊዞች ጋር አብረው መሳሪያ ተቀብለውና ወደ ኢትዮጵያ የናፒየር ጦርን መንገድ በመምራት ስለተጫወቱት ሚና ኢህዴን ትንፍሽ ሳይል በተጨማሪም በጎጃምና በወሎ ያደረሱትን ጥፋት ደብቆ የአማራን ወጣቶች በት/ት ቤት ስለ ዮሀንስ ጀግንነት ብቻ እያስተማረ በሱዳን ድንበር ያለችውን የመውጫና

መግቢያ ቦታ መተማን ዮሀንስ ብሎ በመሰየምና ትግሬወችን በማስፈር ለሕወሀት "ታላቅ ትግራይ" ራእይ እውን መሆን ሌት ተቀን የአጥፍቶ ጠፊ አቅሙን በማራመድ ላይ ተጠምዶ ይገኛል። ሌላም የሆነ ተጨባጭ ማስረጃ ላቅርብላችሁ። የዛሬ 5 አምት አካባቢ ለብዙ ግዜ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በግለሰብ እጅ ተቀምጦ የቆየውና አጼ ምኒልክ በህይወት በነበሩበት ወቅት ለቅዳሴና ለመሳሰለው ሀይማኖታዊ ጸሎቶች ይጠቀሙበት የነበረው የግል መጽሀፍ ቅዱስን ይዘው በመኪና ወደ ጎረቤላ ከተማ ይጉዋዙ ለነበሩት አሜሪካዊ ፕሮፌሰርና አብሩዋቸው የነበሩትን እንጂኔር ተረፈ ራስ ወርቅንና ሌሎችንም እጅግ በጣም ብዙ የአንኮበር ሕዝብ በየመንገዱ ተኮልኩሎ በሆታና በእልልታ አቀባበል አድርጎላቸው ነበር። በወቅቱም ርክክቡ ከወረዳው ሀላፊዎችና ከሸዋ ሀገረ ስብከት ሀላፊዎች ጋር ሲደረግ ቢያንስ በ 6ሚሊዮን ብር ወጪ እዚያው የምኒልክን ሙዚየም ለመገንባት ቃል ሲገባ ሕዝቡ ስሜቱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ደስታውን ገልጾ ነበር። ታዲያ የምኒልክ ስም ሲነሳ የሚደነብረው ኢህዴን አዝማሚያው ስላላስደሰተው ሙዚየሙ እንዳይገነባ በሰጠው ትዛዝ መሰረት የሙዚየሙ ጉዳይ እስካሁን እውን ሊሆን አልቻለም።

ባለፉት 24 አመቶች የአድዋ ድል በአል አከባበር ተዳፍኖና ትብያ ለብሶ ባለበት ሁኔታ አብዛኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች የተወከሉበትን ድል አድራጊ ጦር ያስተባበሩትንና ቆራጥ አመራራቸውን በተግባር በማስመስከር የጥቁር ሕዝቦችን የነጻነት ችቦ ያቀጣጠሉትን አጼ ምኒልክ በቅጥፈት በተሞላ የፈጠራ "ታሪክ" ጥላሸት በመቀባት ኦህዴድ አርሲ ውስጥ ማለትም አማራው በርሱና በኦነግ በተጨፈጨፉበት ዞን የ "አኖሌ" ን ሀውልት ሲያስመርቅ አማራውን እየቀጠቀጠ የሚገዛው ኢህዴን የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ሀላፊውን ከባህርዳር ቦታው ድረስ ልኮ በአደባባይ በምረቃው ላይ ኢህዴንን ወክሎ እንዲሳተፍ በማድረግ ለአማራው ያለውን ጠላትነት አስመስክሩዋል።

ይሄው ጉደኛ ቡድን በክልሉ ለተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ወዘተ፡ ስለ አገሪቱ ሁኔታ "ልማታዊና የሰላም መንግስት" ስለሚባለው ወያኔ ሁሉንም በማስገደድ "ስልጠና" በሚል ሽፋን "አማራውን ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ፣ ሌሎች ብሔረሰቦችን በጭቆናና በግፍ ከ100 አመት በላይ ይገዛ የነበረ ሕዝብ ስለሆነ ባሁኑ ግዜ የተቀሩትን ብሔሮች ይቅርታ እየጠየቀ መኖር አለበት" እያለ በካድሬዎቹ የአማራውን ቅስም ለመስበር ተንቀሳቅሱዋል። በዚህ የ"ስልጠና" መርሀ ግብር በመላው የአገሪቱ ክልሎች የአማራውን መፈናቀል፣ ጭፍጨፋና የንብረት ዝርፊያ በተመለከተ ኢህዴን የሚለው የሚከተለውን ነው። " በመሰረቱ አማራው በሌሎች አገር ሄዶ የመስፈር መብት የለውም። ግን አማራው በታሪክ አጋጣሚ ሀይል ስለነበረው ብሔር ብሔረሰቦችን በጉልበት ዘምቶባቸው መብታቸውን በመግፈፍ የራሱን ቋንቋ፣ ባህልና ሀይማኖት ጭኖ በጭቆና ገዝቱዋቸዋል። ስለዚህም ጨቋኝ ብሔር ነበር። ሕወሀት ነጻ ሲያወጣቸው አማራው ያደርስባቸው የነበረውን በደል ምላሽ የሰጡበት መንገድ ካገራቸው እንዲወጣ ማድረግ ነበር፤ ለዚህም ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም፤ በተጨማሪም አማራው የሚሰፍረው አውዳሚ በሆነ መልኩ ነው፤ ማለትም የተፈጥሮ ደኖችን በእሳት በማቃጠልና በመመንጠር ይህ ነው የማይባል ጥፋቶች በኖረባቸው ክልሎች አድርስዋል፤ ስለዚህ ካለው ትምክህት ጋር ተደምሮ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር አብሮ የመኖር ባህል ስለሌለው ለደረሰበት ችግር ተጠያቂው እራሱ ነው።"

በተለይም የአጼ ምኒልክ አስተዳደር "ጨፍጫፊ፣ ሰው በላና ኤርትራን ለጣሊያን አሳልፎ ሰጥትዋል" የሚሉ ቆርጦ ቀጥል ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የክልሉ ሕዝብ "ምኒልክን እንደ ጥቁር የታሪክ ጠባሳ እንዲቆጥራቸው በእርሳቸውም እንዳይመካ ብሎም ምኒልክ ለአማራው ሀፍረት ናቸው" ብሎ ድምዳሜ በመስጠት በግልጽ ቅስቀሳ አካሂዱዋል። በአንጻሩ ደግሞ ስለ ወያኔ "የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች ከባርነትና ድህነት አማራውን ጨምሮ ነጻ ያወጣው ሕወሀት ስለሆነ ሁሉም የክልሉ ሕዝብ የወያኔን ታሪክ እንዲዘክሩትና እንዲያወድሱት በጥብቅ ከማስጠንቀቅያ ጭምር ማሳሰቢያ ለስልጠናው ተሳታፊዎች ሰጥትዋል።

ዛሬ አማራ ውስጥ ያሉ ት/ት ቤቶች አማራው ላይ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ማለትም በዮዲት ጉዲት፣ በግራኝ አህመድ፣ በኦሮም ወረራ፣ በፋሽሽት ጣልያንና በሌሎችም ስለ ደረሱበት የሕይወት፣ ታሪካዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ጥፋቶች እንደዚሁም የግዛት ወይም ሰፋፊ መሬቶች ዝርፊያ ወዘተ. ማስተማርና መናገር "ሽብርተኛ" በሚባለው የወያኔ ሕግና ደንብ ስለሚያስቀጣ በጉዳዩ ማንም ትንፍሽ እንዳይል "አንድ ለ 5“ በሚባለው የስለላ ድር ከላይ እስከ ታች ተውትበዉታል።

ባጭሩ ታዳጊ የአማራ ተወላጅ ህጻናት ስነ ልቦናዊ አመለካከታቸውና ስለ ማንነታቸው በጠንካራ ታሪካዊ መሰረት ላይ እንዳይታነጽ፤ በድቡሽት ላይ መሰረቱ እንደተጣለ ቤት ተልካሻና ፈራሽ ብሎም ተሸናፊነትንና የበታችነት ስሜት ያላቸው ሆነው በማደግ ለመብታቸው፣ ለማንነታቸውና ሕልውናቸው ተባብረውና በቁጣ ተንገብግበው የመታገል ፍቅር እንዳይኖራቸው የሚያደርግ የት/ት ስራት ተቀርጾላቸው ላለፉት 23 አመቶች ስለተማሩ አዲሱ የአማራ ትውልድ እንዲኮላሽ በኢህዴን በኩል እየተሰራ ያለው የሕወሀትን አላማ የማሳካት ጉዳይ በቀላሉ ታይቶና የት ይደርሳል በሚል የሚታለፍ ክስተት ስላልሆነ ያገባኛል የምንል ሁሉ ይህን መሰሪ ጥፋት ለማብከን ቆርጠን መነሳት እንደሚኖርብን በመረዳት ሳናወላዳ እንቅስቃሴ መጀመር አለብን።

በተለይም ባሁኑ ወቅት የአማራ ወጣቶች ንቃተህሊና ሙሉ በሙሉ በወያኔና ኢህዴን ፕሮፓጋንዳና የት/ት ቤት ስልጠና ስለ መሰለቡ በርካታ መረጃዎች አመላካች ናቸው። ስለ አማራው ታሪካዊ አሰፋፈርና ግዛት፣ ስለ ጥንት አባቶቻቸው ታሪክ፣ ስለ መብታቸው፣ እርስ በርሳቸው በማንነታቸው „አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል“ የሚል አቅም፤ ስለ ቋንቋቸው፣ ስለ ባህላቸው፣ እንደ ትግሬ ወጣቶች ወይም እንደ ኦሮሞ ልጆች ፍቅር ያላዳበሩ በመሆናቸው አማራው ከየክልሉ ሲፈናቀልና በማንነቱ ሲመታ እንደዚሁም የጎንደር መሬቶች በትግሬዎች ሲወረርና ሲቀማ በባለቤትነት ጉዳዩ የራሴ ስለሆነ ይቆረቁረኛል በሚል ስሜት ሲነሱና ሲንቀሳቀሱ አይታዩም። ይህ ማለት ወጣቶቹ የተደቀነባቸውን ጥፋት ማየት የተሳናቸውና የማንነት ችግር ያለባቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ አማራው ራሱን ለማዳን በሚያደርገው ትግል ስኬት ሊያመጣ የሚችለው የወጣቱን ንቃት በማስተካከል የመራራው ትግል ተካፋይ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ሲቻል ብቻ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል።

በሁሉም ክልሎች ወያኔ ካቋቋማቸው ፓርቲዎች ሌላ ተቃዋሚ ነን የሚሉ በርካታ ኅሳን ያነገቡ ድርጅቶች ተመስርተው ሲንቀሳቀሱ ማየት የተለመደ ሆኖ ሳለ አማራውን እታደጋለሁ ብሎ የሚንቀሳቀስ አንድም ድርጅት አለመኖሩ የሚያመላክተው ሕወሀትና ኢህዴን ከሁሉም አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ በአማራው ላይ ፍጹም የሆነ የአምባገነን ፋሽሽታዊ አገዛዝ የዘረጉበት መሆኑንና የነቁ አማራዎች ተደራጅተው እንዳይታገሉ ያለባቸውን ክፉና አስፈሪ የታሪክ አጋጣሚ ነው። "ታሪክ ራሱን ይደግማል ሲሉ" አይ ውሸት ነው እያልኩኝ አልፈው ነበር፤ ነገር ግን አሁን በአማራው እየደረሱ ያሉትን ዘርፈ ብዙና የተቀነባበሩ ጥፋቶች ስመለከት ዮዲት ጉዲትና ሌሎቹም በወያኔ ተተክተው በኔ እድሜ ዘመን ሳይ አቅሜን እንድለውጥ አስገድዶኛል።

ይህ ዘመን ያለንበትን ግዜ በአርቆ አስተዋይነትና በጥልቀት እንድንመረምር ሳንወድ በግድ ያስገድደናል። ዋነኛውና አንገብጋቢው ጉዳይ አማራ ይጥፋ? ወይስ እንዳይጠፋ እንታደገው? የሚሉት አፍጠው እይተመለከቱን ያሉ ሀቆች ናቸው። ስለዚህ መፍትሄው ምን መሆን እንዳለበት በማያወላውል መንገድ የአማራ አድን ዘመቻ ከመጀመር ውጪ ሌላ አማራጭ ካለ ግልጽ ሆነን ምርጫችንን መወሰን ያለብን እኛው አማራዎች መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ሰይፈ ሚካኤል